የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ጥር /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የተመደበለትን መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ**

1. የደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ለቴሌኮሙኒኬሽን የፍጆታ ክፍያ በድምሩ ብር 704,921.46 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

2. መ/ቤቱ ለለቀቁ ሠራተኛ ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ብር 4,483.00 ተገኝቷል፡፡

3. የበጀት ዓመቱን ሳይጠብ ለተፈጸመ የቤት አበል ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ በድምሩ ብር 724,309.80 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

4. የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ ከአንድ አቅራቢ ለተፈጸመ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 68,899.49 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሣያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

5. በግዥ መመሪያው መሠረት የግዥ ዕቅድ ይዘትን ተከትሎ ያልተዘጋጀ የግዥ ዕቅድ በኤጀንሲው የቀረበ መሆኑ፤

6. በሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛ በጀት ብር 39,252,944.75 ተገኝቷል ፤

**ሌሎች ጉዳዮች**

7. በበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ ቢደረግም ተመዝግቦ ከወጪ ቀሪ ያልተረጋገጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡
8. በኤጀንሲው ንብረት ክፍል ውስጥ 8 Dell laptop ,1 HP laptop , 33 Toshiba and 2 Lenovo laptop በድምሩ 44 ላፕቶፖች እንዲሁም 45 Dell desk top እንዲሁም 22 ፕሪንተር በጠረጴዛ ላይና በወለል ላይ ተደራርበ ተቀምጠ ተገኝቷል፡፡
9. የቋሚ ንብረት በሞዴል 19 ሲገባም ሆነ በሞዴል 22 ሲወጣ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ያለመመዝገቡ ታውቋል፡፡

10. የሰሌዳ ቁጥር 4-01888 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር በሊብሬና በመኪናው አካል ላይ ልዩነት መኖሩ (በሊብሬ ላይ የሞተር ቁጥሩ 1HZ0403254 በተሽከርካሪው አካል ላይ 0403384 ) ሆኖ ተገኝቷል፡፡

11. የሰሌዳ ቁጥር ቁ. 4-15351 ሸ. 8 ላንድ ክሩዘር ቶዮታ ሊብሬ የሌለው መሆኑ ታውቋል፣

ከሠላምታ ጋር

---------------------------

ቀን 02/06/2012

ትዕግስት ረታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር